# የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር

## ረቂቅ መመሪያ ቁጥር …/2017

ረቂቅ

መጋቢት 2017 ዓ.ም

## ማውጫ


ገጽ

መግቢያ ..... 1

ክፍል አንድ ..... 1

ጠቅላላ ..... 1

1. አጭር ርዕስ ..... 1
2. ትርጓሜ ..... 1
3. የተፈፃሚነት ወሰን ..... 3

ክፍል ሁለት ..... 3

ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ..... 3

4. የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪነት ለመሰማራት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ..... 3
5. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት ..... 3
6. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕድሳት ..... 4
7. የአድራሻ እና የባለቤትነት ለውጥ ስለማድረግ ..... 4
8. ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት ስለ መስጠት ..... 4
9. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አቀማመጥ ..... 5

ክፍል ሦስት ..... 5

የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ..... 5

10. የግብርና ሜካናይዜሽን የኪራይ አገልግሎት ሰጪ ሰው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ..... 5
11. የግብርና መሳሪያ ጥገና ሰጪ ሰው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ..... 6

ክፍል አራት ..... 6

ስለ ግብርና ሜካናይዜሽን ባለሙያና ቴክኒሽያን ..... 6

12. የባለሙያና ቴክኒሽያን ብዛት ..... 6
13. የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ ..... 7
14. ባለሙያ እና ቴክኒሺያንን ስለመመዝገብ ..... 7

ክፍል አምስት ..... 7

ስለ ኢንስፔክተሮች ..... 7

15. የኢንስፔክተሮች ሥልጣንና ተግባር ..... 8

ክፍል ስድስት ..... 8

አስተዳደራዊ እርምጃዎች አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ ..... 8

16. ማስጠንቀቂያ ስለ መስጠት ........ 8
17. ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማገድ ........ 8
18. ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ ........ 9
19. የግብርና መሳሪያ ስለማገድ ........ 9
20. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመመለስ ........ 9
21. ስለ ቅሬታ አቀራረብ ........ 10
ክፍል ሰባት ........ 10
መረጃ የመያዝ ግዴታ፣መረጃ ለሕዝብ ይፋ ስለ ማድረግ ........ 10
22. መረጃ ስለ መያዝ ........ 10
23. መረጃ ለሕዝብ ይፋ ስለማድረግ ........ 10
ክፍል ስምንት ........ 10
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ........ 10
24. የመሸጋሪያ ድንጋጌ ........ 10
25. መመሪያውን ስለማሻሻል ........ 11
26. የመተባበር ግዴታ ........ 11
27. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች ........ 11
28. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ........ 11
ዕዝሎች ........ 12

## መግቢያ

የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪዎችን የምዝገባ እና የቁጥጥር ሥርዓትን እና ግልፅነት፣ ተደራሽነትና ተጠያቂነትን ያለው አሰራርን በመዘርጋት ከግብርናው ዘርፍ የሚገኘውን ጠቀሜታ ለማሳደግ፤ ጥራቱን የጠበቀ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪውን ዕውቅና በመስጠት የሚያበረታታ፤ ለተጠቃሚው የሚቀርበው አገልግሎትም በመመሪያ ተደግፎ ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገበት እንዲስፋፋ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፡-

የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባርን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 19 ንኡስ አንቀጽ 4 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 1/ (ሸ) እንዲሁም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባወጣው የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 509/2011 ላይ የተደነገጉትን ኃላፊነቶች ለማስፈጸም የግብርና ሚኒስቴር ይህን "የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ እና ቁጥጥር መመሪያ" አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

**ይህ መመሪያ "የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ቁጥጥር መመሪያ" ቁጥር ......./2017 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡**

### 2. ትርጓሜ

በደንብ ቁጥር 509/2014 አንቀፅ 2 ሥር ለተመለከቱ ቃላት የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነው የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "አዋጅ" ማለት የአስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባርን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 1263/2014 ነው፤
2. "ደንብ" ማለት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን አደረጃጀት ስልጣንና ተግባራትን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 509/2014 ነው፤
3. "ሚኒስቴር" ማለት የግብርና ሚኒስቴር ነው፤
4. "የግብርና ሜካናይዜሽን" ማለት በሰው ሀይል፣ በእንስሳት፣ ወይም በሞተር ሃይል የሚንቀሳቀሱ፣ የግብርና ስራዎችን ውጤታማነት የሚያሳድጉ፣ የሰው ጉልበትን የሚቀንሱ፣ ጊዜን የሚቆጥቡ መሳሪያዎችን እና የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም ሂደት ነው፤
5. "የግብርና መሳሪያ" ማለት በግብርና ምርት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል የግብርና ማሽን ወይም የግብርና መገልገያ ዕቃን የሚያካትት ነው፤
6. "የግብርና ማሽን" ማለት በነዳጅ፣ በኤሌክትሪክ፣ ወይም በታዳሽ የሀይል ምንጭ የሚንቀሳቀስ ለግብርና ስራ አገልግሎት የሚውል ማለትም ትራክተር፣ ማጨጃ፣ አጭዶ መውቂያ፣ መውቂያ፣ መፈልፈያ፣ ኬሚካል መርጫ፣ ለመስኖ ልማት የሚውሉ ፓምፕ፣ ለወተት፣ ለዓሣ፣ ለዶሮ፣ ለንብና

ለሐር እንዲሁም ለእንስሳት ልማት የሚውሉትንም ሆነ የግብርና ምርቶችን ለማዘጋጃ፣ ማጓጓዣና ማቀነባበር ስራ የሚያስፈልጉትን፣ ለእንሰሳት መኖ ዝግጅት፣ ለአፈርና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ልማት የሚያገለግሉትን እና ሌሎች ተመሳሳይ ማሽኖችን የሚያካተት ነው፤

7. "አነስተኛ ማሽን" ማለት ለግብርና ስራ አገልግሎት የሚውሉ ከ20 የፈረስ ጉልበት በታች ያለው የግብርና ማሽን ሆኖ ባለ አራት እግር ትራክተሮችን አይጨምርም፤
8. "የግብርና መገልገያ" ማለት በግብርና ማሽን ወይም በእንሰሳት ላይ የሚገጠም ወይም በሰው ጉልበት የሚሰራ የግብርና ስራን ለማከናወን የሚያገለግል ዕቃ ነው፤
9. "የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት" ማለት የግብርና ሜካናይዜሽን ኪራይ ወይም የመሳሪያ ጥገና ስራ ለተጠቃሚው ሰው የሚሰጥበት አሰራር ነው፤
10. "የግብርና ሜካናይዜሽን ኪራይ" ማለት በግብርና መሳሪያ የሚከናወን አገልግሎትን ከአገልግሎት ሰጪ ለተጠቃሚ ሰው የሚሰጥበት አሰራር ነው፤
11. "የግብርና መሳሪያ ጥገና" ማለት በግብርና መሳሪያ ላይ የሚያጋጥመውን የቴክኒክ ጉድለት ለማሟላት በመሳሪያ ክፍል ላይ የሚከናወን የማስተካከያ አገልግሎት ነው፤
12. "ወርክሾፕ" ማለት የግብርና መሳሪያ ጥገና ወይም ሌሎች የማስተካከያ ስራዎች የሚከናወንበት መሰረታዊ ቁሳቁሶችና መሳሪያ የተሟሉበት ቦታ ነው፤
13. "የአገልግሎት ብቃት ተለጣፊ ምልክት" ማለት ተጠቃሚዎች የሜካናይዜሽን አገልግሎት ግዢ በሚፈጽሙበት ወቅት ስለአገልግሎት ሰጪው አስፈላጊውን ግንዛቤ እንዲያውቁ የሚያስችል ከብቃት ማረጋገጫ ጋር የተገናዘበ መረጃን የያዘ፣ በባለስልጣኑ የሚዘጋጅና በመሳሪያው ላይ የሚለጠፍ ምልክት ነው፤
14. "አገልግሎት ሰጪ" ማለት የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎትን ለተጠቃሚ የሚሰጥ ሰው ነው፤
15. "ኢንስፔክተር" ማለት የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት አሰጣጥን ለመቆጣጠር በባለስልጣኑ የሚመደብ ባለሙያ ነው፤
16. "ኦፕሬተር" የግብርና መሳሪያዎችን በተገቢው ሁኔታ ለማንቀሳቀስ፣ ለመጠቀም እና ለመንከባከብ የሚችል የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያለው ነው ፤
17. "ቴክኒሽያን" ማለት የግብርና ሜካናይዜሽን መሣሪያ ላይ በኦፕሬተርነት፣ በጥገና፣ በብየዳ ወይም በኤሌክትሪሺያን ስራ ላይ ለመስራት የሚያበቃ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም ወይም በቀድሞው የትምህርት አሰጣጥ በዲፕሎማ የተመረቀ ወይም አግባብ ያለው የሥራ ልምድ ያለው ወይም ተፈላጊ የትምህርት ዝግጅት ሳይኖረው በብየዳ ወይም በጥገና ወይም በሜካኒክነት የሙያ መስኮች አግባብነት ያለው የስራ ልምድ ያለው እና የሙያ ብቃቱ በምዘና የተረጋገጠ ሰው ነው፤
18. "ባለሙያ" ማለት በግብርና ምህንድስና፣ በግብርና ሜካናይዜሽን ምህንድስና፤ በግብርና መሣሪያ ምህንድስና ወይም በተዛማጅ የትምህርት መስክ ዲግሪና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያለው ሰው ነው፤
19. "አስተዳደራዊ እርምጃ" ማለት በባለሥልጣኑ ወይም ባለሥልጣኑን በሚወክል አካል የሚወሰድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ የብቃት ማረጋገጫ ዕገዳ ወይም ስረዛ ወይም የመሳሰሉትን እርምጃዎች የሚያካትት ነው።
20. "የአገልግሎት ጥራት" ማለት አገልግሎት ሰጪዎች ለአገልግሎት ፈላጊዎች አስፈላጊውን የግብርና ስታንዳርድን ያሟላ አገልግሎት መሰጠቱን የሚረጋገጥበት ስርዓት ነው፤
21. "የአገልግሎት ደህንነት" ማለት አገልግሎት ሰጪዎች ለግብርና ስራ ጥቅም ላይ የሚያውሏቸው መሳሪያ በምርት፣ በክምችትና በማጓጓዝ ሂደት ላይ ጉዳት ከሚያደርሱ ወይም ከሚያውኩ ተፈላጊ ያልሆኑ የዕጽዋት ወይም የእንስሳት ዝርያ ወይም ኬሚካል ነጻ መሆኑን የሚገልጽ ነው፤

22. "የመሳሪያ ጥራት" ማለት አገልግሎት ሰጪ ጥቅም ላይ የሚያውለው መሳሪያ የግብርና ጥራት ስታንዳርድ ማሟላቱን የሚገለጽበት ነው፤
23. "የመሳሪያ ደህንነት" ማለት መሳሪያው በሰውም ሆነ በአካባቢ ላይ ጉዳት የማያስከትል መሆኑንና የግብርና ደህንነት ስታንዳርድ ማሟላቱን የሚገለጽበት ነው፤

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎትን ከአንድ ክልል በላይ በሚሰጥ ሰው የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና ቁጥጥር ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

### 4. የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪነት ለመሰማራት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ

1. በግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ስራ ላይ ለመሠማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በቅድሚያ በሕግ ሥልጣን ከተሰጠው አካል የንግድ ስራ ፈቃድ ማግኘት አለበት፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪነት ለመሰማራት የሚፈልግ ሰው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊኖረው ይገባል፡፡

### 5. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ማንኛውም ሰው በግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪነት ለመሰማራት የሚያስችል አስፈላጊ የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-
   ሀ. እንደአገልግሎቱ ዓይነት በዚህ መመሪያ ክፍል 3 ከተዘረዘሩት መስፈርቶች ውስጥ ድርጅቱ የብቃት ማረጋገጫ የጠየቀበትን መስፈርቶች ማሟላት፤
   ለ. በዚህ መመሪያ የተያያዘውን የማመልከቻ ቅጽ (ዕዝል 1) በመሙላት በአካል ወይም በኢ-ሰርቪስ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ፤
   ሐ. ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም፡፡
2. የአመልካቹ ቅድመ ሁኔታና ዝግጅት የተሟላ ከሆነ ድርጅቱ ከሁለት አባላት ያላነሰ በባለሥልጣኑ የሚመደብ የባለሙያ ቡድን እንዲታይ ይደረጋል፤
3. አመልካቹ አስፈላጊውን መስፈርት ስለማሟላቱ በባለሥልጣኑ ባለሙያዎች ሲረጋገጥ እና ሲጸድቅ በባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ይደረጋል፤
4. በባለሙያ ቡድን ብቁነቱ ያልተረጋገጠ ሰው ሲያጋጥም ፈቃዱ የማይሰጥበት ምክንያት በጽሑፍ እንዲደርሰው ይደረጋል፤
5. ድርጅቱ በጽሑፍ የተሰጠውን መስፈርት አስተካክሎ መገኘቱ ሲረጋገጥ ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል እንደገና ታይቶና ተረጋግጦ የምስክር ወረቀቱ ሊሰጠው ይችላል፤

6. በዚህ አንቀጽ፤ ንዑስ አንቀጽ 1 በተጠቀሰው መሠረት የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የበጀት አመቱ እስኪያልቅ ድረስ የጸና ይሆናል፤
7. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ እንደአግባቡ በሕትመት ወይም በዲጂታል ዘዴ የተዘጋጀ ሊሆን ይችላል፡፡

## 6. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕድሳት

ማንኛውም የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊታደስለት የሚችለው፡-

1) በወቅቱ ይዞት የሚገኘው የምስክር ወረቀት ታግዶ ወይም ተሰርዞ ካልሆነ ወይም አገልግሎት ሰጪው በራሱ ፈቃድ ሥራውን ካላቋረጠ፣
2) ባለሥልጣኑ ለዚህ ሥራ ዘርፍ ያወጣቸው መስፈርቶች የተጠበቁ ስለ መሆናቸው በባለስልጣኑ ባለሙያዎች በዓመታዊ የአሠራር ክትትል ሲረጋገጥ፣
3) አገልግሎት ሰጪው ለዕድሳት አገልግሎት አሰጣጥ አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ ሲከፍል እና በየዓመቱ ለዕድሳት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ (ከሐምሌ 1 እስከ ታህሳስ 30 ባሉት ቀናት) ለዕድሳት ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ፣
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ሳይታደስ የቀረ እንደሆነ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፤
5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አገልግሎት ሰጪው ሥራው መቀጠል ከፈለገ የተቀመጡትን መመዘኛዎች ስለማሟላቱ በባለሥልጣኑ ባለሙያዎች ሲረጋገጥ አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማውጣት ይችላል፡፡

## 7. የአድራሻ እና የባለቤትነት ለውጥ ስለማድረግ

1) ማንኛውም የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ባለስልጣኑን ሳያስፈቅድ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ካገኘበት አድራሻ ወደ ሌላ አድራሻ ማዛወር አይችልም፤
2) በማንኛውም የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ የባለቤትነት ለውጥ ቢያደርግ ቀድሞ የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለባለስልጣኑ መመለስ ይኖርበታል፡፡

## 8. ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት ስለ መስጠት

ቀደም ሲል የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተበላሸበት ወይም የጠፋበት አገልግሎት ሰጪ ምትክ ሊያገኝ የሚችለው፡-

1) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተበላሸበት ከሆነ ከነብልሽቱ የምስክር ወረቀቱን ሲመልስና ምትክ እንዲሰጠው ሲጠይቅ፤
2) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ከሆነ ስለመጥፋቱ የሚገልፅ ማረጋገጫ ከሚመለከተው አካል ሲያቀርብና ምትክ እንዲሰጠው ሲያመለክት፣
3) ለምትክ አሰጣጡ አስፈላጊውን የአገልግሎት ክፍያ ሲከፍል ብቻ ይሆናል፡፡

## 9. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አቀማመጥ

1) ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዋናውን ወይም ቅጅውን በሚጠየቅበት ጊዜ ማቅረብ በሚቻልበት አካባቢ ማስቀመጥ አለበት፤
2) ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ተለጣፊ ወረቀት አገልግሎት በሚሰጥበት ማሽን ላይ መለጠፍ ይኖርበታል፡፡

# ክፍል ሦስት
# የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

## 10. የግብርና ሜካናይዜሽን የኪራይ አገልግሎት ሰጪ ሰው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

1) ማንኛውም ሰው በግብርና ሜካናይዜሽን የኪራይ አገልግሎት ሰጪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በዚህ አንቀጽ፤ ከንዑስ አንቀጽ 2 እስከ 6 የተዘረዘሩትን መሠረታዊ መስፈርቶች በዕዝል 2 በተገለጸበት መልኩ አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፤
2) አገልግሎት ሰጪው የሚሰማራበትን የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት አይነት፣ አላማና የአገልግሎት መዳረሻ፤ ስለሚጠቀማቸው መሳሪያ፣ ስለ ሰው ሀይል መረጃ በዝርዝር የሚገልጽ የስራ ዕቅድ ማቅረብ አለበት፤
3) በዚህ አንቀጽ፤ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ለአገልግሎት ጥቅም ላይ ለሚውል መሳሪያ የሚከተሉት ማሟላት አለበት፤

   ሀ. የመሳሪያው ማረጋገጫ ሰነድ ዋናውና ፎቶ ኮፒ፤

   ለ. መጠለያ፤

   ሐ. በእያንዳንዱ መሳሪያ ውስጥ መፍቻ፤ ግሪስ ማጠጫ እና የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ፤

   መ. አስፈላጊ የማሽን ኦፕሬተር፣ የጥገና ባለሙያ እና የግብርና ሜካናይዜሽን አስተባባሪ መሟላት አለበት፡፡

4) ባለሙያና ቴክኒሺያንን ከአደጋ ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለመጠበቅ የሚያስችላቸው አልባሳት፤ የእሳት አደጋ መከላከያ በእያንዳንዱ ማሽን ላይ፣ በመሳሪያ መጠለያ እና በመጋዘን መውጫ በሮች ላይ
5) ለንጽህና መጠበቂያ በቂ ውሀ፣ ሻወር፣መታጠቢያና መጸዳጃ ለወንድና ለሴት ተለይቶ፤ ቁሳቁስ የተሟላለት ክፍል ወይም ቢሮ፣
6) በዚህ አንቀጽ፤ ከንዑስ አንቀጽ 2 እስከ 5 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ለአነስተኛ ማሽን ወይም ከ75 የፈረስ ጉልበት በታች በሆነ አንድ ትራክተር ብቻ የኪራይ አገልግሎት ስራ ለሚያከናውኑ የሚከተሉትን መስፈርቶች በዕዝል 3 በተገለጸበት መልኩ ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፤

   ሀ. የማሽን ሰነዶች ዋናውና ፎቶ ኮፒ፤

   ለ. እንደአግባቡ የማሽን ኦፕሬተር ወይም ስልጠና ያገኘ ሰራተኛ፤

   ሐ. ማሽን መፍቻ፤ ግሪስ ማጠጫ እና የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ በእያንዳንዱ ከቦታ ቦታ በራሱ በሚንቀሳቀስ መሳሪያ ውስጥ፤

መ. ቴክኒሺያንን ከስራ ላይ አደጋ ለመከላከልና ጤንነትን ለመጠበቅ የሚያስችል የተሟላ አልባሳት መኖር አለበት፡፡

## 11. የግብርና መሳሪያ ጥገና ሰጪ ሰው የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

1) ማንኛውም ሰው በግብርና ሜካናይዜሽን መሳሪያ ጥገና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በዚህ አንቀጽ ከንዑስ፤ ከንዑስ አንቀጽ 2 እስከ 7 የተዘረዘሩትን መሠረታዊ መስፈርቶች በዕዝል 4 በተገለጸበት መልኩ አሟልቶ መገኘት ይጠበቅበታል፤
2) የግብርና መሳሪያ የጥገና ወርክሾፕ፤
3) ጥገናው የተጠናቀቀና ለአገልግሎት ዝግጁ ለሆነ መሳሪያ ማቆሚያ የሚሆን መጠለያ፤
4) አስፈላጊ የጥገና፤ ኤሌክትሪሺያን እና በያጅ ቴክኒሽያን፤
5) የግብርና መሳሪያ መለዋወጫ ዕቃ የሚቀመጥበት ክፍል፤
6) ቴክኒሺያንን ከስራ ላይ አደጋ ለመከላከልና ጤንነትን ለመጠበቅ የሚያስችል የተሟላ አልባሳት መኖር አለበት፤ የእሳት አደጋ መከላከያ፣ አደጋ ሲከሰት የማንቂያ ጥሪ ማድረጊያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ የመሰብሰቢያ ቦታ፤ የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ቁሳቁስ የያዘ ሳጥን መኖር አለበት፤
7) ለንጽህና መጠበቂያ በቂ ውሀ፣ ሻወርና መፀዳጃ ቤት፤ ቁሳቁስ የተሟላለት ክፍል ወይም ቢሮ፤ አመላካች የተጻፈበት ወይም የተለጠፈበት የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ሊኖረው ይገባል፡፡

# ክፍል አራት

# ስለ ግብርና ሜካናይዜሽን ባለሙያና ቴክኒሽያን

## 12. የባለሙያና ቴክኒሽያን ብዛት

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 እና 11 መሰረት አገልግሎት ሰጪ የሚያስፈልገው ዝቅተኛ የባለሙያና ቴክኒሽያን ቁጥር አገልግሎት ሰጪው በሚኖረው የማሽን ቁጥር የሚወሰን ሆኖ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 2 እስከ 7 ከተዘረዘሩት አስፈላጊ ባለሙያና ቴክኒሽያን አንዱን እንዲያሟላ ይጠበቅበታል፤
2) ስለመሳሪያው አያያዝና አጠቃቀም ስልጠና ያገኘ አገልግሎት ሰጪ ቁጥሩ ባልተወሰነ በአነስተኛ ማሽን እና ባለሁለት እግር ትራክተር ላይ አገልግሎት መስጠት ይችላል፣
3) በግብርና ሜካናይዜሽን የኪራይ አገልግሎት ሰጪ ያለው የማሽን ቁጥር አምስት ወይም ከአምስት ያነሰ ከሆነ በማሽኖቹ ቁጥር ልክ ኦፕሬተር፤
4) በግብርና ሜካናይዜሽን የኪራይ አገልግሎት ሰጪ ያለው የማሽን ቁጥር ከአምስት በላይ ከሆነ ኦፕሬተር በማሽኖቹ ቁጥር ልክ፣ በተጨማሪ አንድ የጥገና ቴክኒሽያን እንዲሁም አንድ የሜካናይዜሽን አስተባባሪ ባለሙያ፤
5) በዚህ አንቀጽ፤ ንዑስ አንቀጽ 2-4 የተጠቀሰው መስፈርት ቢኖርም አንድ ኦፕሬተር በትራክተር እንዲሁም በኮምባይን መስራት የሚያስችል የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት እና የመንጃ ፈቃድ ካቀረበ እንዲሁም ስራዎቹ በተለያየ ወቅት የሚከናወኑ ከሆነ ለአንድ ትራክተር እና ለአንድ ኮምባይን አንድ ኦፕሬተር በቂ ሊሆን ይችላል፡፡
6) ኦፕሬተሩ በባለስልጣኑ የክትትል ወቅት የመንጃ ፈቃዱንና የብቃት ማረጋገጫ ሰርትፊኬቱን የማሳየት ግዴታ አለበት፡፡

7) የግብርና ሜካናይዜሽን የጥገና አገልግሎት ሰጪ ቢያንስ አንድ የእርሻ መሳሪያ ጥገና ባለሙያ፤ አንድ ኤሌክትሪሺያን እና አንድ በያጅ ቴክኒሽያን ሊኖረው ይገባል፡፡

## 13. የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 እና 11 የተዘረዘሩት ባለሙያና ቴክኒሽያን በግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ውስጥ ለመስራት በዚህ በአንቀጽ፤ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 7 የተዘረዘሩትን የትምህርት ዝግጅትና አግባብ ያለው የሥራ ልምድ በማሟላት የቅጥር ውል ማስረጃ ሊኖራቸው ይገባል፤
2) በግብርና ሜካናይዜሽን የኪራይ አገልግሎት ሰጪ ውስጥ የግብርና ማሽኖች ኦፕሬተር ለመሆን የታደሰ መንጃ ፈቃድ፣ በሜካናይዜሽን ዘርፎች ላይ የሰለጠነና በሚሰራበት መሣሪያ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ማቅረብ የሚችል እና ቢያንስ ሁለት አመት የስራ ልምድ ያለው መሆን አለበት፤
3) በግብርና ሜካናይዜሽን የጥገና አገልግሎት ሰጪ ውስጥ የጥገና ቴክኒሽያን ለመሆን በአግሮ መካኒክ፣ በግብርና መሣሪያ መካኒክስ፣ በአውቶሞቲቭ ጥገና ወይም በሌሎች ተዛማጅ ዘርፎች ቢያንስ በደረጃ 3 ተመርቆ የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ማቅረብ የሚችልና ሁለት አመት የስራ ልምድ ያለው፤
4) በግብርና ሜካናይዜሽን የኪራይ አገልግሎት ሰጪ ውስጥ የሜካናይዜሽን አስተባባሪ ለመሆን በግብርና ምህንድስና ወይም በግብርና ሜካናይዜሽን ምህንድስና ወይም በተዛማጅ ዘርፍ በዲግሪ እና ከዚያ በላይ የተመረቀና ቢያንስ አንድ አመት የስራ ልምድ ያለው፤
5) በግብርና ሜካናይዜሽን የጥገና አገልግሎት ሰጪ ውስጥ ኤሌክትሪሺያን ለመሆን በአውቶ ኤሌክትሪክሲቲ፣ ኤሌክትሮ መካኒክስ ወይም ተዛማጅ ሙያ ቢያንስ በደረጃ 3 ተመርቆ የብቃት ማረጋገጫ (ሲኦሲ) ሰርቲፊኬት ማቅረብ የሚችልና ሁለት አመት የስራ ልምድ ያለው፤
6) በግብርና ሜካናይዜሽን የጥገና አገልግሎት ሰጪ ውስጥ በያጅ ለመሆን በጠቅላላ መካኒክስ ወይም ተዛማጅ ሙያ በደረጃ 2 የተመረቀና ቢያንስ ሁለት አመት የስራ ልምድ ያለው፤
7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ከ2-6 የተደነገገው ቢኖርም የትምህርት ዝግጅት ሳያሟላ ቢቀርና ቢያንስ ለአምስት ዓመት በልምድ የተገኘ የብየዳ፣ የኤሌክትሪሺያን ወይም የመካኒክ ስራ ችሎታ ኖሮት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ካቀረበ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

## 14. ባለሙያ እና ቴክኒሺያንን ስለመመዝገብ

1) ማንኛውም በግብርና ሜካናይዜሽን ስራ ለመሰማራት የሚፈልግ ባለሙያ በቅድሚያ ከባለስልጣኑ የሙያ ፈቃድ ማግኘት አለበት፣
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሙያ ፈቃድ የሚፈልግ ባለሙያ ወይም ቴክኒሺያን በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 13 ስር የተዘረዘሩትን መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፣
3) በዚህ አንቀጽ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሙያው ወይም ቴክኒሺያኑ ቀድሞ ይሰራበት ከነበረው ሰው ወይም መ/ቤት ህጋዊ የስራ መልቀቂያ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡

# ክፍል አምስት
# ስለ ኢንስፔክተሮች

## 15. የኢንስፔክተሮች ሥልጣንና ተግባር

1) ባለስልጣኑ የባለስልጣኑን ደንብ እና ይህ መመሪያ መከበራቸውን ለማረጋገጥ ኢንስፔክተሮችን ይመድባል፤
2) በዚህ አንቀጽ፤ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚመደብ ኢንስፔክተር ከንዑስ አንቀጽ  3-10 የተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤
3) የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት በሚሰጥበት የሥራ ቦታ በሥራ ሰዓት በመግባት የቁጥጥር ተግባር የማከናወን፤
4) የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት የሚሰጥ መሳሪያን በማስቆም የቁጥጥር ተግባር የማከናወን፤
5) የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት የሚሰጥ መሳሪያን የጥራት ምርመራ የማድረግ፤
6) የተበከሉ ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት በተጠቃሚው ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ በተጠረጠረ የግብርና መሣሪያ ላይ የደህንነት ምርመራ እንዲካሄድ የማድረግ
7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሰረት የግብርና መሣሪያ የደህንነት ምርመራ ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስ ተለይቶ እንዲቆይ የማድረግ፤
8) ከግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት አሰጣጥ ጋር የተዛመደ ማንኛውንም መዛግብት እና ሰነዶችን መመልከትና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ኮፒ ተደርጎ እንዲሰጠው የማድረግ፤
9) የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ባቀረበው መሣሪያ፣ ባለሙያና ሌሎች በመስፈርቱ ላይ የተገለጹ ሁኔታዎችን አሟልቶ እየሰራ መሆኑን የማረጋገጥ፤
10) በዚህ መመሪያ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቅት ሳይኖረው የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት በሚሰጥ ሰው ላይ ቁጥጥር የማድረግ፤
11) በዚህ አንቀጽ፤ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚመደብ ኢንስፔክተር የባለስልጣኑን መታወቂያ ወይም ደብዳቤ ቁጥጥሩ ለሚካሄድበት ድርጅት ባለቤት ወይም ለህጋዊ ወኪሉ ማሳየት አለበት፡፡

# ክፍል ስድስት
# አስተዳደራዊ እርምጃዎች አወሳሰድና ቅሬታ አቀራረብ

## 16. ማስጠንቀቂያ ስለ መስጠት

1) ማንኛውም የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ የፈፀመው ጥፋት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚያሳግድ ወይም የሚያሰርዝ ካልሆነ በስተቀር ባለስልጣኑ እንደአግባብነቱ የቃል ወይም የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡
2) ባለስልጣኑ በሰጠው ማስጠንቀቂያ መሰረት አስፈላጊውን ማስተካከያ ካላደረገ የብቃት ማረጋገጫው ሊሰረዝ ወይም ሊታገድ ይችላል፡፡

## 17. ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማገድ

1) ማንኛውም የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ሰው ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ማስጠንቀቂያ መስጠት ሳያስፈልግ ባለስልጣኑ ጉድለቶች ወይም ጥፋቶች እስኪስተካከሉ ድረስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ሊያግድበት ይችላል፡፡
ሀ. ባለስልጣኑን ሳያስፈቅድ የቦታ አድራሻ ላይ ለውጥ ካደረገ፤

ለ. መስፈርቱን የማያሟላ ባለሙያ ወይም ቴክኒሽያን በቁጥጥር ወቅት አገልግሎት ሲሰጥ ከተገኘ፤

ሐ. ባለሥልጣኑ በማንኛውም ጊዜ ለሚያደርጋቸው የቁጥጥር ስራዎች እንዳያከናውን እንቅፋት የፈጠረ እንደሆነ፤

መ. የብቃት ማረጋገጫ ከተሰጠባቸው መስፈርቶች መካከል ያጓደለ እንደሆነ፤

ሠ. ድርጅቱ ከሁለት ጊዜ በላይ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት ጉድለቱን ማስተካከል ካልቻለ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የታገደበት የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ሰው የተጣለበት ዕገዳ ሊነሳለት የሚችለው በዚህ መመሪያ መሰረት ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም ድርጅቱ ለዕገዳ ያበቃውን ጥፋት ካረመ ወይም ካስተካከለ ብቻ ነው፡፡

## 18. ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ

1) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያገኘ አገልግሎት ሰጪ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ሊሰርዝበት ይችላል፡፡

ሀ. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተገኘው አለአግባብ መሆኑ ከተረጋገጠ፤

ለ. የብቃት ማረጋገጫው ምስክር ወረቀቱ በማናቸውም መንገድ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ካስተላለፈ፤

ሐ. በአንቀጽ 7 መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ በወቅቱ ካልታደሰ

መ. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 20 ላይ የተቀመጡትን ተመሳሳይ ጥፋቶች ፈፅሞ ሲገኝ ወይም በባለስልጣኑ የተጣለበትን እገዳ በመተላለፍ ስራውን ከቀጠለ፤

ሰ. አግባብ ባለው የመንግስት አካል በስራ ላይ እንዳይቀጥል ንግድ ፈቃዱ ሲሰረዝ ወይም ስራውን በራሱ ፈቃድ ሲያቋርጥ፤

ረ. ባለስልጣኑ አስፈላጊ እና ምክንያታዊ ነው ብሎ ያመነባቸውንና የበላይ ሀላፊ ያጸደቃቸው ሌሎች ተመሳሳይ ጥፋቶች ሲፈፅም ቢያንስ ለ1 ዓመት ለሚደርስ ጊዜ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ሊሰርዝበት ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰረዘበት የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ የተሰረዘ ፈቃድ ሊተካለት የሚችለው በዚህ መመሪያ መሰረት ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም ለስረዛ ያበቃውን ጥፋት ሙሉ በሙሉ በማረምና አዲስ የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠው ጥያቄ ሲያቀርብ ነው፡፡

## 19. የግብርና መሳሪያ ስለማገድ

1) ባለስልጣኑ ማንኛውም የግብርና መሳሪያ ጥራትና ደህንነት ጉድለት አስመልክቶ አጠራጣሪ ሁኔታ ከተገኘ ወይም በፍተሻ ወቅት ችግር መኖሩ ሲረጋገጥ ሊያግደው ይችላል፤

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ተገልሎ የቆየ አስፈላጊውን ምርመራ ተደርጎበት በጥቅም ላይ የማይውል መሆኑ ከተረጋገጠ ሊወገድ ይችላል፡፡

## 20.የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመመለስ

1) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሰጠበት የአገልግሎት ዓይነት እና የስራ አድራሻ ለውጥ ሲያደርግ የቀድሞ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መመለስ አለበት

2) አዲስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ጠይቆ ተቀባይነት ሲያገኝ የቀድሞ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መመለስ አለበት
3) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ከተሰረዘ፣ ከታገደ፣ በተቀመጠው የእድሳት ጊዜ ገደብ ሳይታደስ ከቀረ ወይም በራሱ ፈቃድ ስራውን ካቋረጠ በ15 ቀናት ውስጥ መመለስ አለበት፡፡

## 21. ስለ ቅሬታ አቀራረብ

በባለስልጣኑ በሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ላይ ቅሬታ የሚቀርበው የፌደራል የአስተዳደር ሥነ- ሥርዓትን ለመደንገግ በወጣ አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሰረት ይሆናል፡፡

# ክፍል ሰባት
# መረጃ የመያዝ ግዴታ፣መረጃ ለሕዝብ ይፋ ስለ ማድረግ

## 22. መረጃ ስለ መያዝ

1) ማንኛውም ሰው ከሚሰጠው የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ጋር ተያያዥ የሆኑ ሰነዶችን በአግባቡ የመያዝና በባለስልጣኑ ሲጠየቅም የማሳየት ግዴታ አለበት፤
2) በድርጅቱ ውስጥ ስላለው ሰራተኛ የትምህርት ደረጃ፣ የስራ ልምድ፣ የወሰዱት ስልጠና ዓይነት የሚገልፅ ዝርዝር መረጃ የያዘ ፋይል መኖር አለበት፤
3) በድርጅቱ ውስጥ ስላለው የግብርና መሳሪያ አይነት፣ ብዛት፣ ስለ ማሽንና መሳሪያ ጥገና እና የጥራት ሁኔታ የሚገልፅ ዝርዝር መረጃ የያዘ ፋይል መኖር አለበት፡፡

## 23. መረጃ ለሕዝብ ይፋ ስለማድረግ

1) ባለሥልጣኑ የወሰደውን ማንኛውም አስተዳዳራዊ እርምጃ በተመለከተ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና የቅሬታ አቀራረብ ጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ ወይም ቅሬታ ሰሚ አካሉ ጉዳዩን መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ መረጃዎቹን ለህብረተሰቡ ይፋ ሊያደርግ ይችላል፤
2) ባለሥልጣኑ በማንኛውም አገልግሎት ሰጪ ላይ ያገኛቸው የአሰራር ግድፈቶች፣ የተረጋገጡ ተጨባጭ ጥቆማዎች ሲያገኝ መረጃዎቹን በማንኛውም የመገናኛ ዘዴ ይፋ ሊያደርግ ይችላል፤
3) ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ ምስጢር ተብለው ከተያዙ መረጃዎች በስተቀር አገልግሎት ሰጪዎችን በተመለከተ መረጃ ማግኘት ይችላል፡፡

# ክፍል ስምንት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 24. የመሸጋሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ይደረግ በነበረ የምዝገባ ሂደት ወይም ልማዳዊ አሰራር የተመዘገበ ሰው ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ በዚህ መመሪያ መሠረት ምዝገባ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 25. መመሪያውን ስለማሻሻል

የግብርና ሚኒስቴር አስፈላጊ ሆኖ ባገኘበት በማንኛውም ወቅት ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል።

## 26. የመተባበር ግዴታ

ባለስልጣኑ ይህን መመሪያ ለማስፈፀም እንዲችል ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል መንግሥት አካላት የመተባበር ግዴታ አለበት።

## 27. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ዓይነት መመሪያ፣ ሰርኩላር ደብዳቤ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ ላይ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

## 28.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በግብርና ሚኒስቴር ጸድቆ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት ቀን አንስቶ ተፈጻሚ ይሆናል ።

ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)
የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር

ረቂቅ

**ዕዝሎች**

ዕዝል 1

## የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መጠየቂያ ቅጽ

(በአካል ወይም በኢ-ሰርቪስ)

1. የአመልካቹ ሙሉ ስም ______________________የቀበሌ መታወቂያ/ፓስፖርት (አባሪ ማድረግ)
2. የአገልግሎት ዓይነት _______________________ የንግድ ስም______________________________
3. አመልካቹ በድርጅቱ ውስጥ ያለው ኃላፊነት_______________________________________________
4. የድርጅቱ ባለቤት ሙሉ ስም__________________________________________________________

አድራሻ፣ ክልል ___________________ ክ/ከተማ (ዞን) ወረዳ __________ከተማ_________________
ስልክ ቁ.___________ሞባይል __________________ኢሜይል_________________________________

5. የአገልግሎት መስጫ አድራሻ
ክልል ___________________ከተማ___________ ክ/ከተማ (ዞን) ወረዳ ___________
ስልክ ቁ.___________ ሞባይል __________________ኢሜይል_________________________________
የቦታው ልዩ መጠሪያ_________________________________

ቅርንጫፍ የአገልግሎት መስጫ ቦታዎች_____________________________________________________

6. የአገልግሎት ዓይነት
የግብርና ሜካናይዜሽን፣ የኪራይ አገልግሎት ሰጪ___________፣ የጥገና አገልግሎት ሰጪ__________፣
ሌላ አገልግሎት ከሆነ ይገለጽ፣ ___________፣___________፣___________፣

7. የቴክኒክ ባለሙያ ወይም ሰራተኛ ስም፣ የሙያ አይነት እና የትምህርት ዝግጅት
ስም ---------------------------የሙያ አይነት ----------------------------የትምህርት ዝግጅት-------------------
ስም ---------------------------የሙያ አይነት ----------------------------የትምህርት ዝግጅት-------------------
ስም ---------------------------የሙያ አይነት ----------------------------የትምህርት ዝግጅት-------------------
ስም ---------------------------የሙያ አይነት ----------------------------የትምህርት ዝግጅት-------------------

8. እኔ ________________________ የተባልኩኝ የግብርና ሜካናይዜሽን ኪራይ ወይም ጥገና ወይም ___________አገልግሎት ሰጪ በብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ያሟላሁ ስለሆነ ድርጅቱ ታይቶ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጠኝ እጠይቃለሁ፡፡

ፊርማ ______________________________፣ ቀን __________________________

---

ለቢሮ ሥራ ብቻ የሚያገለግል
*ማመልከቻውን የተቀበለው ባለሙያ ስም* ___________________________________
*ማመልከቻውን የተቀበለበት ቀን* ________________________
*መልስ የሚሰጥበት ቀን (ቀጠሮ)* ___________________________

# የግብርና ሜካናይዜሽን ኪራይ አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ስለመሟላታቸው መገምገሚያ ቅፅ

የድርጅቱ ስም ________________________________________

አገልግሎት ሰጪው የሚገኝበት አድራሻ፡ ክልል __________ዞን/ክፍለ ከተማ _____________

ወረዳ __________ከተማ_________ቀበሌ________የቦታው ልዩ መጠሪያ ______________

ስልክ ቁጥር _________ ሞባይል ____________፣ ኢሜይል፣ ______________

የድርጅቱ ባለቤት ወይም ተወካይ ______________________________

| ተ ራ ቁ. | የመገምገሚያ መስፈርት | ክብደ ት | የተሰ ጠ ነጥብ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ለአገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውል ከቦታ ቦታ ተንቀሳቃሽ የሆነ ማሽን ስለመኖሩና ለዚህም ሊብሬ ወይም ግዢ የተፈጸመበት ሰነድ፣ የመድን ምስክር ወረቀት (የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ) እና አመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ ማረጋገጫ (ቦሎ)፤ወይም ከቦታ ቦታ ተንቀሳቃሽ ያልሆነ ማሽን ስለመኖሩና ለዚህም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ወይም ግዢ የተፈጸመበት ሰነድ ስለመኖሩ | 18 | | |
| 2 | በዚህ መመሪያ ክፍል 4 ስር በተጠቀሰው መሰረት የማሽን ኦፕሬተር፣ የጥገና ባለሙያ እንዲሁም የግብርና ሜካናይዜሽን አስተባባሪ ስለመኖሩ እና አስፈላጊ ሰነድ ስለመቅረቡ | 17 | | |
| 3 | ለአገልግሎት ጥቅም ላይ ለሚውል መሳሪያ ከቆርቆሮ፣ ከእንጨት ወይም ከብሎኬት ሊሰራ የሚችል እና የግንባታው አሰራር በግራና ቀኝ እንዲሁም ከፊት ለፊት ግድግዳ ያለውና በመግቢያ በኩል ክፍት ሆኖ ጣሪያው ቆርቆሮ የለበሰ መጠለያ ስለመኖሩና በማስረጃ ስለመረጋገጡ | 15 | | |
| 4 | በእያንዳንዱ መሳሪያ ውስጥ መሰረታዊ መፍቻ፤ ግሪስ ማጠጫ እና የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ስለመኖሩ | 15 | | |
| 5 | የእሳት አደጋ መከላከያ በእያንዳንዱ ማሽን ላይ፣ በመሳሪያ መጠለያ እና በመጋዘን መውጫ በሮች ላይ ስለመኖሩ | 10 | | |
| 6 | ባለሙያና ቴክኒሺያንን ከስራ ላይ አደጋ ለመከላከልና ጤንነትን ለመጠበቅ የሚያስችል ቱታ፣ ጋዋን፣ ጫማ፣ ኮፍያ፣ ጓንት፣ የአይን መከላከያ፣ ማስክ እና የመሳሰሉት ስለመሟላታቸው | 9 | | |
| 7 | ለንጽህና መጠበቂያ በቂ ውሀ፣ ሻወርና መፀዳጃ ለወንድና ለሴት ተለይቶ ስለመኖሩ | 9 | | |
| 8 | የተለያዩ መዛግብትና ሰነዶችን ለማስቀመጥ (የጥገና፣ የሰርቪስ እንዲሁም የኦፕሬተር ማኑዋልና ካታሎግ) እንዲሁም የጽህፈት ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል ቁሳቁስ የተሟላለት ቢሮ ወይም ክፍል ስለመኖሩ | 7 | | |
| ድምር | | 100 | | |

**ማሳሰቢያ፡** የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ከላይ በሰንጠረዡ ከተቀመጡት መስፈርቶች መካከል በተ.ቁ 1 እና 2 የተገለጹትን የግዴታ መሟላት፤ በአጠቃላይ ቢያንስ 60% ማግኘት ይጠበቃል።**<u>የባለሙያዎች የማጠቃለያ አስተያየት</u>**

______________________________________________________________

| የባለሙያዎች ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| 1.________________ | ________________ | ________________ |
| 2. .________________ | ________________ | ________________ |
| 3.________________ | ________________ | ________________ |

የኃላፊው አስተያየት ________________________________________

ስም ____________________ ፊርማ ____________________ቀን _______________

ዕዝል 3

# የግብርና ሜካናይዜሽን በአነስተኛ ማሽን ወይም በ75 የፈረስ ጉልበት በታች በሆነ አንድ ትራክተር ብቻ የኪራይ አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ስለመሟላታቸው መገምገሚያ ቅፅ

የድርጅቱ ስም ________________________________________________

አገልግሎት ሰጪው የሚገኝበት አድራሻ፡ ክልል __________ዞን/ክፍለ ከተማ _____________

ወረዳ __________ከተማ_________ቀበሌ________የቦታው ልዩ መጠሪያ ______________

ስልክ ቁጥር __________ ሞባይል ____________፣ ኢሜይል፣ ______________

የድርጅቱ ባለቤት ወይም ተወካይ ____________________________________

| ተራ ቁ. | የመገምገሚያ መስፈርት | ክብደት | የተሰጠ ነጥብ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ለአገልግሎት ጥቅም ላይ የሚውል ከቦታ ቦታ በራሱ የሚንቀሳቀስ ማሽን ስለመኖሩና ለዚህም ሊብሬ ወይም ግዢ የተፈጸመበት ሰነድ፣ የመድን ምስክር ወረቀት (የ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ) እና አመታዊ የተሽከርካሪ ምርመራ ማረጋገጫ (ቦሎ) ወይም ከቦታ ቦታ በራሱ ተንቀሳቃሽ ያልሆነ አነስተኛ ማሽን ወይም ባለሁለት እግር ትራክተር ስለመኖሩና ለዚህም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ወይም ግዢ የተፈጸመበት ሰነዶች ዋናውና ፎቶ ኮፒ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ | 25 | | |
| 2 | ከቦታ ቦታ በራሱ ለሚንቀሳቀስ ማሽን የማሽን ኦፕሬተር ወይም በአነስተኛ ማሽን እና ባለሁለት እግር ትራክተር ላይ የሚሰራ ሰራተኛ ስለመሳሪያው አያያዝና አጠቃቀም ስልጠና አግኝቶ የተሳተፎ ማረጋገጫ ወረቀት ስለመኖሩ | 30 | | |
| 3 | ከቦታ ቦታ በራሱ ለሚንቀሳቀስ ማሽን መሰረታዊ መፍቻ፤ ግሪስ ማጠጫ እና የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ በእያንዳንዱ መሳሪያ ውስጥ ስለመኖሩ | 30 | | |
| 4 | ቴክኒሺያንን ከስራ ላይ አደጋ ለመከላከልና ጤንነትን ለመጠበቅ የሚያስችል ቱታ፣ ጋዋን፣ ጫማ፣ ኮፍያ፣ ጓንት፣ የአይን መከላከያ፣ ማስክ እና የመሳሰሉት ስለመሟላታቸው | 15 | | |
| ድምር | | 100 | | |

**ማሳሰቢያ፡** የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ከላይ በሰንጠረዡ ከተቀመጡት መስፈርቶች መካከል በተ.ቁ 1 እና 2 የተገለጹትን የግዴታ መሟላት፤ በአጠቃላይ ቢያንስ 60% ማግኘት ይጠበቃል፡፡

<u>የባለሙያዎች የማጠቃለያ አስተያየት</u>

______________________________________________________________

______________________________________________________________

| የባለሙያዎች ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| 1.____________________ | ____________________ | ____________________ |
| 2. .____________________ | ____________________ | ____________________ |
| 3.____________________ | ____________________ | ____________________ |

የኃላፊው አስተያየት ______________________________________________

ስም ____________________ ፊርማ ____________________ቀን _______________

ዕዝል 4

# የሜካናይዜሽን ጥገና አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ስለመሟላታቸው መገምገሚያ ቅፅ

የድርጅቱ ስም ________________________________________

አገልግሎት ሰጪው የሚገኝበት አድራሻ፡ ክልል __________ዞን/ክፍለ ከተማ______________

ወረዳ __________ከተማ_________ቀበሌ________የቦታው ልዩ መጠሪያ ______________

ስልክ ቁጥር __________ ሞባይል ____________ኢሜይል፣ ______________

የድርጅቱ ባለቤት ወይም ተወካይ ______________________________

| ተራ ቁ. | የመገምገሚያ መስፈርት | ክብደት | የተሰጠ ነጥብ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የግብርና መሳሪያ የጥገና ስራ የሚከናወንበት ቢያንስ በግራና ቀኝ ግድግዳ ያለውና፣ በውስጡ የመጠገኛ ጉድጓድ ያለው ሆኖ ጣሪያው ቆርቆሮ የለበሰ ወርክሾፕ፤ ወርክሾፑ የሚያርፍበት ቦታ የግል ከሆነ የይዞታ ማረጋገጫ፤ የኪራይ ከሆነ ቢያንስ ለአንድ ዓመት የኪራይ ውል ስለመኖሩ | 18 | | |
| 2 | በዚህ መመሪያ ክፍል አራት ስር በተገለጸው መሰረት የጥገና፤ ኤሌክትሪሺያን እና በያጅ ቴክኒሽያንና አስፈላጊ ሰነዶች ስለመኖራቸው | 17 | | |
| 3 | ጥገናቸው የተጠናቀቀ እና ለአገልግሎት ዝግጁ የሆኑ መሳሪያዎች ማቆሚያ የሚሆን ከቆርቆሮ፣ ከእንጨት ወይም ከብሎኬት የተሰራ መጠለያ ስለመኖሩ | 15 | | |
| 4 | የግብርና መሳሪያ መለዋወጫ ዕቃዎች የሚቀመጥበት ክፍል ስለመኖሩ | 15 | | |
| 5 | ቢያንስ አንድ አንድ የእሳት አደጋ መከላከያ በጥገና ቦታ፣ በማሽን መጠለያ ውስጥ እንዲሁም መለዋወጫ ዕቃዎች የሚቀመጥበት ክፍል፤ የእሳት አደጋ መከላከያዎች፣ አደጋ ሲከሰት የማንቂያ ጥሪ ማድረጊያ ደወል እና በአደጋ ጊዜ የመሰብሰቢያ ቦታ ስለመኖሩ | 8 | | |
| 6 | ቴክኒሺያንን ከስራ ላይ አደጋ ለመከላከልና ጤንነትን ለመጠበቅ የሚያስችል ቱታ፣ ጋዋን፣ ጫማ፣ ኮፍያ፣ ጓንት፣ የአይን መከላከያ፣ ማስክ እና የመሳሰሉት ስለመሟላታቸው | 7 | | |
| 7 | ለንጽህና መጠበቂያ በቂ ውሀ፣ ሻወርና መፀዳጃ ቤት ስለመኖሩ | 5 | | |
| 8 | የተለያዩ መዛግብትና ሰነዶችን ለማስቀመጥ (የጥገና፣ የሰርቪስ እንዲሁም የኦፐሬተር ማኑዋልና ካታሎግ) እንዲሁም የጽህፈት ስራዎችን ለመስራት የሚያስችል ቁሳቁስ የተሟላለት ቢሮ ወይም ክፍል ስለመኖሩ | 5 | | |
| 9 | የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ቁሳቁስ የያዘ ሳጥን ስለመኖሩ | 5 | | |
| 10 | አመላካች የተጻፈበት ወይም የተለጠፈበት የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ስለመኖሩ | 5 | | |
| ድምር | | 100 | | |

**ማሳሰቢያ፡** የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ከላይ በሰንጠረዡ ከተቀመጡት መስፈርቶች መካከል በተ.ቁ 1 እና 2 የተገለጹትን የግዴታ መሟላት፤ በአጠቃላይ ቢያንስ 60% ማግኘት ይጠበቃል፡፡

**<u>የባለሙያዎች የማጠቃለያ አስተያየት</u>**

____________________________________________________________

____________________________________________________________

የባለሙያዎች ስም ፊርማ ቀን

1.______________________ ______________________ ____________________

2. .______________________ ______________________ ____________________

የኃላፊው አስተያየት ____________________________________________________

ስም ______________________ ፊርማ ______________________ቀን ___________

ፎቶ

Photo

ዕዝል 5

የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን
Ethiopian Agricultural Authority

ቁጥር………………
ቀን…………………

## የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት
## Certificate of competency for Agricultural Mechanization Service Provider

…………………….. የተባለ ድርጅት የተቀመጠውን ዋና ዋና መስፈርት /የስራ ቦታ፣ የሰው ሃይል፣ አስፈላጊ መሳሪያዎች እና ሌሎች መስፈርቶች/ ስለማሟላቱ በተደረገው ኢንስፔክሽን ተረጋግጦ ይህ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በግብርና ሚ/ር መመሪያ ቁጥር 000/2017 አንቀጽ 00 መሰረት የግብርና ሜካናይዜሽን ኪራይ/ጥገና አገልግሎት ለመስጠት የንግድ ፍቃድ መስጫ መደብ ቁጥር …….. መሰረት ይህ የብቃት ማረጋገጫ ወረቀት ተሰጥቷል፡፡

**This certificate of competency is issued to the trading organization in accordance with the Ministry of Agriculture Directive No. 000/2025 Article No. 00 Business license category number …….. after assuring the fulfilment of basic requirement.**

1. የቢሮ አድራሻ/Address:

   ክልል፡……….ክ/ከተማ፡…………. ወረዳ-…… የቤትቁጥር-….ስልክ:09…….

   Region-……… Subcity-………. Woreda-……House No-…… Mobile-09………

2. አገልግሎት የሚሰጥበት አድራሻ/Address:-

   ክልል፡……….ክ/ከተማ፡…………. ወረዳ-…… የቤትቁጥር-….ስልክ:09…….

   Region-……… Subcity-………. Woreda-……House No-…… Mobile-09………

3. የድርጅቱ ባለቤት ስም ፡ …………..

   Owner's name-…………………

4. የድርጅቱ ባለሙያ ስም፡ …………..

   Company expert name-…………………

ፍቃድ የተሰጠበት ቀን፡ …./…./20… ዓ.ም ያጸደቀው ኃላፊ ፊርማ፡-…………

Issue Date signature of authorized officer

| ታድሷል/Renewed | ታድሷል/Renewed | ታድሷል/Renewed | ታድሷል/Renewed |
|---|---|---|---|
| ቀን ……/……..20…..ዓ.ም | ቀን ……/……..20…..ዓ.ም | ቀን ……/……..20…..ዓ.ም | ቀን ……/……..20…..ዓ.ም |
| ያጸደቀው ኃላፊ | ያጸደቀው ኃላፊ | ያጸደቀው ኃላፊ | ያጸደቀው ኃላፊ |
| ስም…………………….. | ስም…………………….. | ስም…………………….. | ስም…………………….. |
| ፊርማ/sign………………. | ፊርማ/sign………………. | ፊርማ/sign………………. | ፊርማ/sign………………. |